በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
ፍትሕ ቢሮ
የሕግ ምክር፣ማ ርቀቅና ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት

IE AMAHARA NATIONAL REGIONAL STATE
JUSTICE BUREAU
\L COUNSELING, DRAFTING AND COMPILATION
DIRECTORATE

ቁጥር፡- የሕ/ምክ/ማር/ማጠ/1038/18

ቀን 28/04/2018 ዓ/ም

ለአብክመ ትራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ ባለስልጣን

ባህርዳር

ጉዳዩ፡- የመመሪያ ምዝገባን ይመለከታል

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአስተዳደር ሥነ ሥርዓትን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 292/2017 አንቀጽ 16(4) መሰረት ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም አዋጁ ከመውጣቱ በፊት በስራ ላይ የነበሩ መመሪያዎችን አስመልክቶ አዋጁ በወጣ በአንድ ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለፍትህ ቢሮ በመላክ እንዲመዘገብ ማድረግ እንዳለበት ተደንግጓል።

ተቋማችሁ በአዋጁ መሰረት በቁጥር ት/ሎ/ባ/03/-360/18 በቀን 24/03/18 ዓ/ም በተፃፈ ሸኚ ደብዳቤ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ባለሥልጣን የተሸከርካሪ ወቅታዊ የገበያ መሸጫ ዋጋ የግምት አሰራር መመሪያ ቁጥር 21/2017ን የላካችሁልን መሆኑ ይታወቃል።

በእኛም በኩል የተላከልንን ይህን መመሪያ በአዋጁ መሰረት ተመልክተን መመሪያ ቁጥር 21/2017 ተብሎ ይጠራ የነበረውን በመመዝገብ በአዲስ **መመሪያ ቁጥር 35/2018 ዓ/ም** በሚል ሰጥተን የላክንላችሁ መሆኑን እንገልፃለን።

ከሰላምታ ጋር

መስፍን መኮንን

የሕግ ምክር፣ ማርቀቅና ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት
የክልል ዐቃቤ ሕግ

ግልባጭ

- ለቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት፤(ያለ አባሪ)
- ለፍት/ሕግ ጉዳ/ዘር/ምክትል ቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት
  ፍትህ ቢሮ

Tel.No. ☎ 058 220 0794/792 / 058 226 59 90 ✉ 995

# መመሪያ ቁጥር 35/2018 ዓ/ም

# በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ባለሥልጣን የተሽከርካሪ ወቅታዊ የገበያ መሸጫ ዋጋ የግምት አሰራር

የተሽከርካሪ ባለንብረትነት ስም ዝውውር በሚደረግበት ጊዜ በቴምብር ቀረጥ አዋጅ ቁጥር 110/1990 ንዑስ አንቀፅ 3 ቁጥር 12 እና በአንቀፅ 5 ቁጥር 6(ሀ) መሰረት የተሽከርካሪው ወቅታዊ ዋጋ ግምት በማስላት የስም ማዛወሪያ ቀረጥ (የቴምብር ቀረጥ) 2% (ሁለት በመቶ) ባለንብረቱ የሚከፍል ከመሆኑ በተጨማሪ ይህንኑ የተሽከርካሪው ወቅታዊ ዋጋ ግምትን መሰረት አድርጎ በተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 308/2002 እና በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 መሰረት 2 % (ሁለት በመቶ) እና 15% (አስራአምስት በመቶ) (በቅደም ተከተል) ክፍያ የሚከፈል በመሆኑ፤

የገቢ ዓይነቶችን ለመሰብሰብም መነሻ የሚደረገው በትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ባለስልጣን የተሽከርካሪውን ወቅታዊ ዋጋ ግምት በማስላት በሚሰጠው የሰነድ ማረጋገጫ በመመስረት በመሆኑ፤

የትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ባለስልጣን አስልቶ የሚሰጠው የተሽከርካሪ ወቅታዊ የዋጋ ግምት ከገበያው የመሸጫ ዋጋ ጋር የተጣጣመ ባለመሆኑና በዚህም ሳቢያ የክልሉ መንግስት ከዘርፉ መሰብሰብ የነበረበትን ገቢ በእጅጉ ያነሰ ከመሆኑ አኳያና የገቢ ማነስ ዋነኛ ምክንያት ተደርጎ የሚወሰደውም የትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ባለስልጣን የተሽከርካሪ ወቅታዊ የዋጋ ግምትን እየሰራ ያለው የኤፌዲሪ ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለስልጣን ሰኔ 10/1994 ዓ.ም ያወጣውን ዓመታዊ የዋጋ ግሽበት መጠን 0.07 (7%) በማድረጉ፤

ከተሽከርካሪ ሽያጭ የሚሰበሰብ የቴምብር ቀረጥ እና ታክስ ገቢ በተገቢው ሁኔታ ለመሰብሰብ እንዲቻል የሚመለከታቸው የትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ባለስልጣን እና የገቢዎች ቢሮ ባለሙያዎች የተሽከርካሪ የገበያ መሸጫ ዋጋ ግምት አሰራርን በተመለከተ ዳሰሳ ጥናት ተደርጎ የተሽከርካሪ የዋጋ ግምት አሰራር የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት በደ. ቁጥር 1-9-3/112 በቀን 09/01/2017 ዓ.ም ያወጣውን ዓመታዊ የዋጋ ግሽበት መጠን 0.243 (24.3%) መሰረት በማድረግ ማሻሻል በማስፈለጉ፤

በተሻሻለው የግምት አሰራር አደጋ ለደረሰባቸው ተሽከርካሪዎች ከፖሊስ ማስረጃ ሲያቀርቡና ማስረጃው ሲታመንበት የቴክኒክ ባሙያዎች ተሽከርካሪው በአደጋ ምክኒያት ያጣውን ነጥብ በመቶኛ ይሰጣሉ:: ተሽከርካሪው አደጋ ያልደረሰበት ከሆነ ፋይል ውስጥ የሚገኙ መሰረታዊ ታሳቢዎችን እና ሌሎች ማስረጃዎችን በማገናዘብ የተሽከርካሪው የመሸጫ ዋጋ ግምት ይሰራል:: ለዚህ አስፈላጊ የሆኑ አባሪ ማስረጃዎች ከዚህ መመሪያ ጋር ተያይዘዋል። ስለሆነም አገልግሎት አሰጣጡን በዘመናዊ ቴክኖሎጂና አሠራር በመደገፍ ዘርፉን ለማዘመንና ምቹ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ሁኔታ መፍጠር ወሳኝ በመሆኑ፤

በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የትራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ ባለስልጣን ማቋቋሚያ ክልል መስተዳደር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 199/2014 ዓ.ም አንቀጽ 18 መመሪያ መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል::

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የተሽከርካሪ ወቅታዊ የገበያ መሸጫ ዋጋ የግምት አሰራር መመሪያ ቁጥር 35/2015 ዓ/ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

በደንቡ ትርጓሜ የተሰጣቸው ቃላት እንደ አግባቡ በዚህ መመሪያ ተፈጻሚ መሆናቸዉ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ መመሪያ ዉስጥ የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የማይሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ፡-

1/ "ክልል" ማለት የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ነው፤

2/ "ደንብ" ማለት በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የትራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ ባለስልጣን ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 199/2014 ዓ/ም ነው፤

3/ "ባለስልጣን" ማለት የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ባለስልጣን ነው፤

4/ "ግምት (የግምት አሰራር)" ማለት ከነሐሴ 1994 ዓ.ም ጀምሮ የሚሰራበትን የተሽከርካሪዎች የገበያ መሸጫ ዋጋ ግምት ወይም የግምት አሰራር ነው፤

5/ "ታሳቢ (variable)" ማለት በተሽከርካሪዎች የገበያ መሸጫ ዋጋ ላይ ተጽኖ ያላቸው ተለዋዋጭ (የኢኮኖሚ ሂደቶች) ነው፤

6/ "ስያሜ" ማለት ታሳቢዎች የሚወክሉባቸው ምህፃረ ቃላት ነው፤

7/ "ዋ" ማለት የገበያ መሸጫ ዋጋ ስያሜ ነው፤

8/ "ዲ" ማለት የመነሻ ዋጋ (ዲክለራሲዮን) ስያሜ ነው፤

9/ "ግ" ማለት የዋጋ ግሸበት ማስተካከያ ስያሜ ነው፤

10 "እ" ማለት ከእርጅና የሚቀር ዋጋ ስያሜ  ነው፤

11/ "ይ" ማለት የይዘት ተቀናሽ መጠን ስያሜ ነው፤

12/ "ጨ" ማለት አጠቃላይ የተመራጭነት መጠን ስያሜ ነው፤

13/ "ዓ" ማለት የተሽከርካሪው ዓይነት ተመራጭነት ስያሜ ነው፤

14/ "አገ" ማለት የተሽከርካሪው አገልግሎች ዓይነት /ዘርፍ/ ተፈላጊነት ስያሜ ነው፤

15/ "ሀ" ማለት ተሽከርካሪው የተሰራበት ሀገር ተመራጭነት ስያሜ ነው፤

16/ "ፋ" ማለት ተሽከርካሪው የተሰራበት ፋብሪካ ተመራጭነት ስያሜ ነው፤

17/ "በ" የገማች ኮሚቴ ነጥብ /መጠኑ በባለሙያ በመቶኛ የሚሰጥ/ ስያሜ ነው፤

18/ "ኮሚቴ" ማለት ፡ በየደረጃው የሚገኙ የባለስልጣኑ ተቋማት የተሽከርካሪዎችን የገበያ መሸጫ ዋጋ ለመወሰን ኃላፊነት የተሰጠው ኮሚቴ ነው፤

19/ "ዘ" ማለት የተሽከርካሪው የአገልግሎት ዘመን /ዕድሜ/ ስያሜ ነው፤

20/ "ት/ሲ/ግ/መ/ቅ-1" ማለት ትራንስፖርት ሲስተም ግምት መስሪያ ቅጽ-1 ነው፤

21/ "ት/ሲ/ግ/መ/ቅ-2" ማለት ትራንስፖርት ሲስተም ግምት መስሪያ ቅጽ-2 ነው፤

22/ "ት/ሲ/ግ/መ/ቅ-3" ማለት ትራንስፖርት ሲስተም ግምት መስሪያ ቅጽ-3 ነው፤

23/ "ት/ሲ/ግ/ማ/ቅ-4" ማለት ትራንስፖርት ሲስተም የግምት ውጤት ማሳወቂያ ቅጽ-4 ነው፤

24/ "ድርብ ተግባር" ማለት አራት ሰው እና ጭነት /እስከ 10 ኩንታል/ ሚጭኑ ባለ ሁለት ጋቢና ተሽከርካሪዎች የሚሰጡት አገልግሎት ዓይነት ነው፤

25/ "ውስን ነጥብ" ማለት ለግምት መሥሪያ ታሳቢዎች አባሪ ከተደረጉ ሠንጠረዦች የሚይዙት ነጥብ ነው፤

26/ "የቴምብር ቀረጥ" ማለት የስም ዝውውር አገልግሎት ለማግኘት የሚከፈል ቀረጥ ሲሆን መጠኑ የግምት ዋጋውን 2% ነው።

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ ተፈጻሚ የሚሆነው በክልሉ በሚገኙ ማንኛውም ህጋዊ የተሽከርካሪ ምዝገባ ባደረጉ ባለንብረቶች ላይ ነው።

# ክፍል ሁለት

# የግምት አሰራር

## 4. የግምት ዋጋ ስሌትን ለመስራት የሚረዱ መረጃዎችን የሚወክሉ የተለያዩ ታሳቢዎች በሞዴሉ ውስጥ ያላቸው ስያሜና መጠሪያ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር በተቀመጠው ሰንጠረዥ ቀርበዋል።

1/ መሰረታዊ ታሳቢዎች

መሰረታዊ ታሳቢዎች መሰረታዊ መረጃዎችን የሚወክሉ ታሳቢዎች ሲሆኑ፣ ለታሳቢዎች የሚሰጠው ውሱን ነጥብ/ዋጋ በቀጥታ በፋይል ውስጥ ከሚገኙ ሰነዶች ወይም አባሪ ከተደረጉ ሰንጠረዦች ይወሰዳል።

ሰንጠረዥ - 1 *የታሳቢዎች ስያሜ፣ መጠሪያና መረጃ / ነጥብ የሚወሰድበት ሰነድ፦*

| | የታሳቢው መጠሪያ | ስያሜ | መረጃ የሚወሰድበት ፋይል | ነጥብ የሚወሰድበት ቦታ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የአገልግሎት ዘመን(እድሜ) | ዘ | ከዲክላራሲዮን፣ ጨረታ፣ ተመሳሳይ ተሽከርካሪ | ሰንጠረዥ-5 |
| 2 | ከእርጅና የሚቀር ዋጋ | እ | ከዲክላራሲዮን፣ ጨረታ | ሰንጠረዥ-5 |
| 3 | የተሰራበት ሀገር ተመራጭነት | ሀ | Inspection, land certificate | ሰንጠረዥ -3 |
| 4 | የተሰራበት ፋብሪካ ተመራጭነት | ፋ | | ሰንጠረዥ-4 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 5 | የተሽከርካሪው አገልግሎት ተፈላጊነት | አገ | Specification | ሰንጠረዥ-2 |
| 6 | መነሻ ዋጋ ከዲክላራሲዎን | ዲ | ከዲክላራሲዎን፣ጨረታ፣ ተመሳሳይ ተሽከርካሪ | ከዲክላራሲዎን፣ ጨረታ፣ ተመሳሳይ ተሽከርካሪ |
| 7 | የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ | ግ | ከመመሪያ | ሰንጠረዥ- 6 |
| 8 | የይዘት ተቀናሽ መጠን | ይ | ቴክኒክ ማስረጃ | በባለሞያ |

ሀ) ከላይ በተመለከተው ሰንጠረዥ ውስጥ ከተራ ቁጥር 1—7 የተዘረዘሩት መሰረታዊ ታሳቢዎች ሲሆኑ መረጃዎች እና የሚወክሉት ነጥብ /ዋጋ በቀጥታ ከፋይል/ ከአባሪ ሰንጠረዦች በመውሰድ ይሞላል፣

ለ) በተ.ቁ 8 ላይ የተጠቀሰው የይዘት ታሳቢ "ይ" ሲሆን መጠኑ በባለሙያ የሚወሰን ይሆናል፡፡

## 2/ በስሌት ተሰርተው የሚታወቁ ታሳቢዎች

ሀ) "ዓ"

የተሽከርካሪ አይነት የተመራጭነት መጠን የሚሰላው "ሀ" እና "ፋ" ተመራጭነት የሚሰጣቸውን ውሱን ነጥብ አማካይ በመውሰድ ነው፡፡

ይኸውም:-

ሞዴል -1 $ዓ = \frac{(ሀ+ፋ)}{2}$

<u>*ማስታወሻ፡-*</u>

- የ “ ፋ " ውሱን ነጥብ ከሰንጠረዥ 4 ይወሰዳል፡፡
- የ “ ሀ " ውሱን ነጥብ ከሰንጠረዥ 3 ይወሰዳል፡፡

ለ) "ጬ"

ይህ ታሳቢ "አገ"ን በ"ዓ" በማባዛት የሚገኝ ታሳቢ ነው፡፡

ይኸውም:-

ሞዴል -2 ጬ = ዓ X አገ

ማስታወሻ ፡-

- የ "ዓ" መጠን በሞዴል -1 ተሰርቶ የሚገኝ ነጥብ ነው፡፡
- የ "አገ" ውሱን ነጥብ ከሰንጠረዥ - 2 ይወሰዳል፡፡

## ሐ) "ዋ"

ይህ ታሳቢ ተሽከርካሪው በወቅቱ ገበያ ላይ የሚሸጥበትን ዋጋ ግምት የሚወክል ታሳቢ ነው፡፡ የመሸጫ ዋጋ ግምት በሞዴል መሰረት ተሰልቶ የሚገኝ የዋጋ ግምት ነው፡፡ ይህ ዋጋ በተዋዋዮች ከሚቀርበው ዋጋ ጋር ተነፃፅሮ ከፍተኛው የቴምብር ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ይሆናል፡፡ ይህ ታሳቢ ከሚከተሉት ሞዴሎች በአንዱ ይሰራል፡፡

(1) አደጋ ያልደረሰባቸው ተሽከርካሪዎች የመሸጫ ዋጋ ግምት መስሪያ

ሞዴል፡-

ሞዴል - 3 ዋ = (ዲ + (ዲX15%)) X ጨ X ግ X እ

(2) አደጋ የደረሰባቸው ተሽከርካሪዎች የመሸጫ ዋጋ ግምት መስሪያ ሞዴል፡

ሞዴል - 4 ዋ = (ዲ + (ዲX15%)) X ጨ X ግ X (እ - ይ)

ሞዴል - 5 ይ = (እ - 0.25) X በ

ማስታወሻ

- "ዲ" በፋይል ውስጥ ከሚገኙ ሰነዶች/ የዲክለራሲዮን/ የጨረታ/ የሚወሰድ ታሳቢ ነው
- "ግ" የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ "ግ" መጠን የተሽከርካሪውን እድሜ "ዘ" መሰረት በማድረግ ከሰንጠረዥ -6 የሚወሰድ ታሳቢ ነው፡፡
- "ጨ" በሞደዴል -2 መሰረት የሚሰላ ታሳቢ ነው፡፡
- "በ" ከገማች ኮሚቴ የይዞታ መግለጫ ቅፅ የሚወሰድ ታሳቢ ነው፡፡

## 5. በባለሙያ የሚገመቱ ታሳቢዎች

ተሽከርካሪ ማርጀት ከነበረበት ዘመን በተለይ ሁኔታ ዋጋ ሊያሳጡ የሚችሉ አደጋዎችን መጠን ለማስላት የባለሙያ እገዛ አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታ ነው። ተሽከርካሪዎች በአደጋ ምክንያት ያጡትን የዋጋ መጠን "ይ" የባለስልጣኑ የገማች ኮሚቴ የአደጋውን መጠን በ ት/ሰ/ግ/መ/ቅ-3 ቅፅ ከሞላ በኂ፣ በሞዴል 5 አማካኝነት የሚሰላ ታሳቢ ነው። አደጋ የደረሰባቸውና የፖሊስ ማስረጃ የሚቀርብባቸው ተሽከርካሪዎች ማስረጃው በመምሪያ / በባለስልጣኑ ኃላፊ ሲታመንበት ተሽከርካሪው በአደጋ ምክንያት ያጣውዋጋ መጠን በባለስልጣኑ ሦስት (03) ባለሙያዎች እንዲጣይ ይደረጋል።

1/ የገማች ኮሚቴው የነጥብ አሰጣጥ ከዚህ በታች በቀረበው እና ት/ሰ/ግ/መ/ቅ-3 መሰረት ይሆናል፦

ሀ) የይዘት ተቀናሽ ታሳቢ "ይ" ከእርጅና የሚተርፈውን የተሽከርካሪ ዋጋ "እ" እና የገማች ኮሚቴ ነጥብ "በ" መሰረት በማድረግ ይሆናል። የገማች ኮሚቴ ነጥብ ዋጋ በመቶኛ የሚሰጥ ሲሆን ይህም የተሽከርካሪውን ዋና ዋና አካላት እና ንዑስ አካላትን
መሰረት በማድረግ የሚሰጥ ይሆናል፣

ለ) ተሽከርካሪው የሚሰራ ሆኖ በተሽከርካሪው የተለያዩ ክፍሎች ላይ የደረሰው ጉዳት መጠነኛ ከሆነ ተሽከርካሪው ያለበትን ሁኔታ በማገናዘብ የገማች ኮሚቴ ነጥብ "በ" አጠቃላይ ድምር ከ5%—30% ይሰጠዋል፣

ሐ) ተሽከርካሪው /መሳሪያው የማይሰራ ሆኖ በተለያዩ ክፍሎች ላይ የደሰው ጉዳት ከፍተኛ ከሆነ ተሽከርካሪው ያለበትን ሁኔታ በማገናዘብ ከ31%—80% የገማች ኮሚቴ ነጥብ "በ" ይሰጠዋል፣

መ) ተሽከርካሪው የማይሰራ ከሆነና የተሽከርካሪው ዋና ዋና አካላት ሙሉ በሙሉ ከጥቅም ውጭ ከሆኑ የገማች ኮሚቴው ነጥብ "በ" ከ81%—100% ይሰጠዋል፣

ሠ) የአገልግሎት ዘመን ጣሪያ የደረሱ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ተሽከርካሪዎች መሳሪያዎች የይዘት ተቀናሽ መጠን ዜሮ የሚሰጠው ሲሆን፣ የአገልግሎት ዘመን ጣሪያ እንደሚከተለው ይሆናል፦

(1) የህዝብና የጭነት ተሽከርካሪዎች የአገልግሎት ዘመን ጣሪያ 25 ዓመት፣
(2) የሞተር ሳይክልና የትራክተር የአገልግሎት ዘመን ጣሪያ 10 ዓመት፣
(3) አጭዶ መውቂያ እና ሌሎች የአገልግሎት ዘመን ጣሪያ 15 ዓመት።

ረ) በት/ሲ/ግ/መ/ቅ-3 ተሞልቶ ለግምትክፍል የሚላከው የገማች ኮሚቴ ነጥብ "በ" መሰረት በማድረግ የይዘት ተቀናሽ መጠን "ይ" በሞዴል - 5 መሰረት ይሰራል፣

ሰ) የተሽከርካሪው የመሸጫ ዋጋ ግምት በሞዴል - 4 መሰረት ይሰላል።

## 6. የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ

በኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት በደ.ቁ 1-9-3/112 በቀን 09/01/2017 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ በተገለፀልን መሰረት ከነሀሴ 01/2015 ዓ.ም እስከ ሐምሌ 30/2016 ዓ.ም የነበረውን ምግብ ነክ ያልሆኑ ሸቀጦች የአመቱን አማካይ የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ መጠንን 0.243 (24.3%) የምጠቀም ሲሆን ይህ ዋጋ በተሽከርካሪው የአገልግሎት እድሜ ከተባዛ በኋላ 1.00 (አንድ) ነጥብ በመጨመር/ በመደመር የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ መጠን ሆኖ ይወሰዳል፡፡

ይኸውም ፡-

ሞዴል-6 ግ=(ዘ X 0.243) + 1.00

**የዋጋ ግምት ማስተካከያ የሚደረግበት ጊዜ**

- አመታዊ አማካይ የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ በየ 1 ዓመቱ አንድ ጊዜ የሚታደስ ይሆናል፡፡

**ማስታወሻ**

- "ግ" የተሽከርካሪውን የአገልግሎት ዘመን መሰረት በማድረግ ከሰንጠረዥ -6 ይወሰዳል፡፡

## 7. ስለ ታሳቢዎች ውስን ነጥብ አወሳሰድ

በዚህ አንቀጽ ስር የተቀመጡት የሚከተሉት ሠንጠረዦች የታሳቢዎች ውስን ነጥብ የሚወሰድባቸው ናቸው፡-

1/ ሠንጠረዥ -2 የተሽከርካሪው አገልግሎት ዓይነትና መጠን ተፈላጊነት "አገ"፦

| ተ.ቁ | | የአገልግሎት አይነት | ነጥብ /አገ/ |
|---|---|---|---|
| 1 | ሀ | የህዝ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች:<br>➢ አውቶቡስ(ከ11 ሰው በላይ )<br>➢ የመስክ(Station wagen)እና<br>➢ የድርብ ተግባር(Pick Up) | 1 |
| | ለ | የጭነት ተሽከርካሪዎች:የደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል በላይ የሚጭኑ | |
| 2 | ሀ | አውቶሞቢል እስከ 4ሰው | 0.97 |
| | ለ | አውቶቢስ እስከ 12 ሰው(Van) | |
| | ሐ | የጭነት ተሽከርካሪዎች:<br>• 10 ኩንታል ና ከዚያ በታች የሚጭኑ<br>• የፈሳሽ ጭነት እና<br>• ተሳቢ ማንኛውም አይነት | |
| 3 | ሀ | ሞተር ሳይክል ከ4 ሰው በታች | 0.95 |
| | ለ | የእርሻ መሳሪያዎች | |
| | ሐ | መሳሪያ የተገጠመባቸው | |
| | መ | ሌሎች ከላይ ያልተገለፁ | |

2/ ሠንጠረዥ -3 ተሽከርካሪው የተሰራበት ሀገር ተመራጭነት ውስን ነጥብ "ሀ"፦

| ተ.ቁ | | የተሰራበት ሀገር | ነጥብ /ሀ/ |
|---|---|---|---|
| 1 | ሀ | አውሮፓ | 1 |
| | ለ | አሜሪካ | |
| | ሐ | ጃፓን | |
| 2 | ሀ | ራሽያ | 0.98 |
| | ለ | ኮሪያ | |
| | ሐ | ደቡብ ኮሪያ | |
| 3 | ሀ | ቻይና | 0.95 |
| | ለ | ህንድ | |
| | ሐ | አፍሪካና ሌሎች | |

3/ ሠንጠረዥ -4 ተሽከርካሪውን ያመረተው ፋብሪካ ተወዳጅነት ውሱን ነጥብ "ፋ"፦

| ተ.ቁ | ሰንጠረዥ 4 የተሸከርካሪ አይነት | | የተሰራበት ፋብሪካ | ነጥብ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አውቶሞቢል፣ የመስክ(Station wagen)፣ ድርብ ተግባር(Pick up)፣ አውቶቢስ ትንሽ(ከ12 ሰው በታች)(Van) | ሀ | መርሰዲስ፣ቢምደብሊው፣ ቼቭሮሌት፣ ቮልቮ፣ ቶዮታ፣ፈራሪ | 1 |
| | | ለ | ፔጆ፣ካዲላክ፣ላንድሮቨር፣ቮልስ | 0.98 |
| | | ሐ | ፊያት፣ሚትስቡሽ፣ኦፔል፣ሬኖ፣ኒሳን፣ አይሱዚ፣ላዳ፣ ሱዚኪ፣ ፎርድ፣ ሆንዳ | 0.95 |
| | | መ | ዲህትሱ፣ሀውንዳይ፣ ኦራንዲ፣ዳው፣ጂፕ፣ ኒቫ | 0.9 |
| | | ሠ | ዋዝ፣ ሊትሮይን፣ አውዲ፣ ሱባሮ፣ ቫርፐ፣ ቫፋሮ፣ ዳቺያ፣ማዝዳ እና ሌሎች | 0.85 |
| 2 | አውቶቢስ ትልቅ(Autobis)፣ የጭነት (ደረቅና ፈሳሽ)(Dam Track, lobed testabi, tesabi, Crane, Crane track, fire engine, Rig, Mixer, Fork lift) | ሀ | መርሰዲስ፣ቮልስ፣ኢቪኮ፣ዳፍ፣ፊያት፣ስካኒያ፣ አይሱዙ | 1 |
| | | ለ | ሂኖ፣ቶዮታ፣ ኒሳን፣ ሚትስቡሺ | 0.98 |
| | | ሐ | ዳው፣ ማክ፣ ኬኖርዝ፣ ላይለንድ፣ካላብሪዝ | 0.95 |
| | | መ | ካማዝ፣ ዋዝ፣ ኡራል፣ ጋዝ፣ ጂፋንግ፣ ኤሉስ፣ ብላክ እና ሌሎች | 0.9 |
| 3 | ሞተር ሳይክል (Bajaj) | ሀ | ያምሀ፣ ሱዚኪ፣ ቢምደብሊው | 1 |
| | | ለ | ሆንዳ | 0.9 |
| | | ሐ | ባጃጅ፣ ሽሪፍ፣ኡራል እና ሌሎች | 0.8 |
| 4 | ትራክተር፣ ማጨጃና መውቂያ፣የአፈር መግፍያ | ሀ | ሲፈርግሰን፣ ጆንዲር፣ ካተርፒላር፣ ጆልቮ፣ ስካይ፣ ሚችግን፣ አይናፓክ፣ የማገኢንገር፣ ሶልራንግድ፣ሀይስተር፣ አስላስኮፒክ፣ዳማግ፣ ኤዲጃ | 1 |
| | | ለ | ፊያት፣ ዝማይ፣ ኢ512፣ኢ614፣ ሂታያ፣ ኮማትሱ፣ቫይብሮ፣ ማስከስ፣ማሪኒ | 0.9 |
| | | ሐ | አይም2፣ዲ2፣ ኒቮስኬ5፣ ሚትስቡሽ፣ ደሬሰር፣ ሞብኮ፣ ጋልዮን፣ ካዝ፣ 2ሲኤም፣ ፍሩካዋ፣ ቤቴል፣ ሀም፣ ፊያት፣ ኢሊስ፣ ቻምፒዮን፣ ሀማንና ሌሎች | 0.8 |

4/ ሠንጠረዥ -5 ከእርጅና ቀሪ ዋጋ "እ"፦

| የአግልግሎት ዘመን | ከእርጅና የሚቀር ዋጋ (እ) | | |
|---|---|---|---|
| | የህዝብና የጭነት ተሽከርካሪ | ሞተር ሳይክልና ትራክተር | ማጨጃና መውቂያ |
| 1 | 0.94 | 0.85 | 0.90 |
| 2 | 0.91 | 0.80 | 0.85 |
| 3 | 0.88 | 0.75 | 0.80 |
| 4 | 0.85 | 0.70 | 0.75 |
| 5 | 0.82 | 0.65 | 0.70 |
| 6 | 0.79 | 0.60 | 0.65 |
| 7 | 0.76 | 0.55 | 0.60 |
| 8 | 0.73 | 0.50 | 0.56 |
| 9 | 0.70 | 0.45 | 0.52 |
| 10 | 0.67 | 0.40 | 0.48 |
| 11 | 0.65 | " | 0.44 |
| 12 | 0.63 | " | 043 |
| 13 | 0.61 | " | 0.42 |
| 14 | 0.59 | " | 0.41 |
| 15 | 0.57 | " | 0.40 |
| 16 | 0.55 | " | " |
| 17 | 0.53 | " | " |
| 18 | 0.51 | " | " |
| 19 | 0.49 | " | " |
| 20 | 0.47 | " | " |
| 21 | 0.45 | " | " |
| 22 | 0.43 | " | " |
| 23 | 0.42 | " | " |
| 24 | 0.41 | " | " |
| 25 | 0.40 | " | " |

<u>ማስታወሻ</u>

የህዝብና የጭነት ተሽከርካሪ ከ1-10 ዓመት አገልግሎት ዘመን ሲቀነስ (-0.03)፣ ከ11-22 ዓመት አገልግሎት ዘመን ሲቀነስ(-0.02) እና ከ23-25 ዓመት አገልግሎት ዘመን ሲቀነስ(-0.01) ሞተር ሳይክልና ትራክተር ከ1-10 ዓመት አገልግሎት ዘመን ሲቀነስ (-0.05) እንዲሁም ማጨጃና መውቂያ ከ1-7 ዓመት አገልግሎት ዘመን ሲቀነስ (-0.05)፣ ከ8-11 ዓመት አገልግሎት ዘመን ሲቀነስ (-0.04) እና ከ12-15 ዓመት አገልግሎት ዘመን ሲቀነስ (-0.01) በማስላት የሚሰራ ውጤት ነው።

የአገልግሎት ዘመናቸው የህዝብና የጭነት ተሽከርካሪ 25 ዓመት፣ ሞተር ሳይክልና ትራክተር 10 ዓመት እና ማጨጃና መውቂያ 15 ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆናቸው ተሽከርካሪዎች የእርጅና ቅናሽ ማስተካከያ እ = 0.40 በቋሚነት ይወሰዳል።

5/ ሰንጠረዥ -6 የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ "ግ"፦

| የአገልግሎት ዘመን | የአሁኑ የዋጋ ግሽበት(ግ) |
|---|---|
| 1 | 1.243 |
| 2 | 1.486 |
| 3 | 1.729 |
| 4 | 1.972 |
| 5 | 2.215 |
| 6 | 2.458 |
| 7 | 2.701 |
| 8 | 2.944 |
| 9 | 3.187 |
| 10 | 3.43 |
| 11 | 3.673 |
| 12 | 3.916 |
| 13 | 4.159 |
| 14 | 4.402 |
| 15 | 4.645 |
| 16 | 4.888 |
| 17 | 5.131 |
| 18 | 5.374 |
| 19 | 5.617 |
| 20 | 5.86 |
| 21 | 6.103 |
| 22 | 6.346 |
| 23 | 6.589 |
| 24 | 6.832 |
| 25 | 7.075 |

ማስታወሻ

የአገልግሎት ዘመናቸው 25 ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆናቸው የህዝብና የጭነት ተሽከርካሪዎች የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ ግ = 7.075 በቋሚነት ይወሰዳል፡፡ አመታዊ አማካይ የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ በአመት አንድ ጊዜ የሚከለስ ይሆናል፡፡

ግ = (ዘ x 0.243) + 1

# ክፍል ሦሥት

## የመፍትሄ ሀሳቦች

## 8. በግምት አሰራር ወቅት የሚገጥሙ ችግሮች እና የሚወሰዱ የመፍትሄ ርምጃዎች

1/ ተሸከርካሪው በመጀመሪያ የተመዘገበው ሌላ ክልል ሁኖ በፋይሉ ውስጥ ምንም የጉምሩክ መነሻ ዋጋ የሌለው ከሆነ ተሸከርካሪው ከዚያ በኋላ ተሸጦ ከሆነ የቅርብ ጊዜ ሽያጭ የግምት ዋጋ እና ዓ.ም መውሰድ፤ ይህም በቋሚነት የመነሻ ዋጋ በመሆን ያገለግላል፡፡ የጉምሩክም ሆነ የሽያጭ ማስረጃ ታሪክ ከሌለው በተመሳሳይ ተሸከርካሪ ፋይል ውስጥ የሚገኝን ማስረጃ መጠቀም ይቻላል፤

2/ ተሽከርካሪው ለግምት ሲቀርብ የጉምሩክም ሆነ የቴምብር ቀረጥ ያልተከፈለበት ሁኖ ገዥ የነፃ መብት ያለው ካልሆነ የጉምሩክም ሆነ የቴምብር ቀረጥ መክፈል አለበት፡፡ የሚከፍለው የቴምብር ቀረጥ መቶኛ የጉምሩክ ቀረጥ በከፈለበት ጊዜ በነበረው መቶኛ ይሆነል፡፡ ከዚያም ሸጥኩ ብሎ በ ቀረበው ውልና በገዛበት ዋጋ ጉምሩክ የገመተው መቅረጫ ቀረጡ እና የቴምብር ቀረጥ ተደምሮ የበለጠው ዋጋ ግምት ይወሰዳል፤

3/ የሽያጭ ውል በወጭ ገንዘብ ተጠቅሶ ሲቀርብ ወደ ሀገር ውስጥ ገንዘብ በሳምንት በሚሰራው የምንዛሬ መጠን (ሬት) ተቀይሮ ተዋዋዮች ያቀረቡት ዋጋ ይሆናል፤

4/ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ የግምት ማሳወቂያ ጥያቄ እና የውርስ ጥያቄ በሚቀርብበት ጊዜ፡-

ሀ) በፋይሉ ውስጥ የሚገኙ አስፈላጊ መረጃዎች ከተለቀሙ በኋላ ስሌቱ ይሰራል፤

ለ) ግምቱ ከተረጋገጠ በኋላ ለፍ/ቤቱ በደብዳቤ ለውርስ ከሆነ የግምት ዋጋው በግምት ማስታወቂያ ላይ እንዲሞላ ከተደተረገ በኋላ የቴምብር ቀረጡ እንደተከፈለ ማህተም በማድረግ እንዲረጋገጥ ይደረጋል፡፡

5/ ባለጉዳዮች ተሸከርካሪያቸውን ጋራዥ በማቆም ሲጠይቁ፣ ተሽከርካሪዎች ቢሮ ቀርበው ከሚከፈለው የማስገመቻ ዋጋ እጥፍ በማስከፈል የገማች ኮሚቴው በመስሪያ ቤቱ ትራንስፖርት በመጠቀም በፕሮግራም እንዲታይ ይደረጋል፤

6/ ከአስመጭ ድርጅቶች አዲስ ተሽከርካሪ ተገዝቶ ፋክቱር ወይም የሽያጭ ውል ይዞ ሲቀርብ፡-

ሀ) በፋክቱር ላይ ያለውን ዋጋ እና የጉምሩክ ክፍያዎችን የጠቅላላ ዋጋ ድምር (ዲክለራሲዮን) ዋጋ በማነፃፀር የሚበልጠው የቴምብር ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ይሆናል፤

ለ) ፋክቱሩ ላይ ያለው ዋጋ አነስተኛ ከሆነ ልዩነቱን ሻጭ ኩባንያው የሚጠየቅበት በመሆኑ የዲክለራሲዮን እና የፋክቱር ፎቶ ኮፒ በመውሰድ በፋይል ውስጥ እንዲያያዝ ይደረጋል።

7/ በጅምላ የገቡ ተሽከርካሪዎች ዋጋ እና የጉምሩክ ቀረጥ ክፍያ በጅምላ የተሰራ ከሆነ፡-

ሀ) የቴምብር ቀረጡ ለተሽከርካሪው ተለይቶ የተሰራ ከሆነ ወደ መቶኛ በመቀየር የሚገኘውን ዋጋ መውሰድ፤

ለ) የተመሳሳይ ተሽከርካሪዎች ዋጋ እና የጉምሩክ ቀረጥ ክፍያ በጅምላ የተሰራ ከሆነ ዋጋዎቹን አንድ ላይ ደምሮ በተሽከርካሪውች ብዛት እኩል በማካፈል ድርሻውን መውሰድ፤

ሐ) የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋቸው ተለይቶ ተሰርቶ ከሆነ የእያንዳንዱን የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ እና ቀረጥ አንድ ላይ ከተደመረ በኋላ የቴምብር ቀረጥ ማውጣት ከዚያም በኋላ ቀረጡን እና የቴምብር ቀረጥ የተሰራበትን ዋጋ በመደመር እንደመነሻ (ዲክለራሲዮን) ዋጋ መውሰድ ይገባል።

8/ የቀረጥ ነፃ መብት ኑሮት ነገር ግን ቴምብር ቀረጥ ነፃ መብት የሌለው ከሆነ፣ የቴምብር ቀረጥ የጉምሩክን የመቅረጫ ዋጋን መሰረት በማድረግ እንዲከፍል ይደረጋል። የጉምሩክ ቀረጥ ሲከፍል የቀረጡን 2% የቴምብር ቀረጥ እንዲከፍል ይደረጋል፤

9/ የቴምብር ቀረጥ ነፃ መብት ሳይኖረው የቴምብር ቀረጥ ሳይከፍል ተመዝግቦለት የነበረ ከሆነ፣ተሽከርካሪው በተመዘገበበት ወቅት በነበረው የቴምብር ቀረጥ መቶኛ መክፈል አለበት፤

10/ ሻጭ የጉምሩክ እና የቴምብር ቀረጥ ነፃ መብት ኑሮት ገዥ ነፃ የጉምሩክ ቀረጥ ብቻ ነፃ መብት ያለው ከሆነ ገዥ ብቻ የቴምብር ቀረጥ ይከፍላል፤

11/ ሻጭም ገዥም የቴምብር ቀረጥ ነፃ መብት ያላቸው ከሆነ የቴምብር ቀረጥ ሳይከፍሉ የስም ዝውውር ይደረጋል፤

12/ ከባል ወደ ሚስት ወይም ከሚስት ወደ ባል የሚተላለፍ ከሆነ የሚከፈለው የቴምብር ቀረጥ የተሽከርካሪውን ግማሽ የዋጋ ግምት መሰረት በማድረግ ሆኖ ከላይ ከተጠቀሰው ውጭ የሚተላለፍ ከሆነ የቴምብር ቀረጥ የተሽከርካሪውን ሙሉ ዋጋ መሰረት በማድረግ የሚከፈል ይሆናል፤

13/ በጨረታ የተገዛ ተሽከርካሪከ ሲሸጥ የጨረታ ዋጋ እና የተከፈለው የቴምብር ቀረጥ እንደመነሻ ዋጋ (ዲክለራሲዮን) ይወሰዳል፤

14/ ተሽከርካሪው በጋራ ባለቤትነት የተያዘ ሁኖ አንደኛው የጋራ ባለቤት ያለውን ድርሻ ለሌላው የጋራ ባለቤት ላልሆነ ግለሰብ ወይም ሰው ሲያስተላልፍ፡-

ሀ) የቴምብር ቀረጥ የሚከፈለው በንብረቱ ሙሉ ዋጋ ላይ ሳይሆን በተላለፈው ድርሻ ላይ ብቻ መሰረት በማድረግ ይሆናል፤

ለ) በጋራ ባለቤትነት በተያዘ ንብረት ላይ እያንዳንዱ ባለሀብት ያለውን ድርሻ የሚገልፅ ማስረጃ በንብረቱ ላይ የጋራ ሀብትን ያቋቋመው ውል ወይም ኑዛዜ ነው፤

ሐ) ውሉ ወይም ኑዛዜው የእያንዳንዱን ባለሀብት ድርሻ የማያመላክት ሲሆን እያንዳንዱ የጋራ ባለሀብት በንብረቱ ላይ እኩል ድርሻ እንዳለው ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

15/ የሻንሲ ወይም የሞተር የማስገመቻ ጥያቄ ሲቀርብ የቴምብር ማስከፈያ ዋጋ፡-

ሀ) ለሻንሲ፡- የተሽከለርካሪውን ጠቅላላ ዋጋ 32% መውሰድ ይሆናል፤

ለ) ለሞተር፡- የተሽከርካሪውን ጠቅላላ ዋጋ 25% መውሰድ ይሆናል፡፡

16/ በአዲሱ የግምት አሰራር ወይም ከነሀሴ 14/1994 ዓ.ም ጀምሮ ተሽከርካሪውን ያስገመተ ሁኖ ግምቱ 6 ወር ያልሞላው ከሆነ የቴክኒክ ምርመራ ሳይደረግ አገልግሎት እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡ ሆኖም 6 ወር እና ከዚያ በላይ የሆነው ተሽከርካሪ የቴክኒክ ምርመራ በማድረግ የግምት አገልግሎት ያገኛል፡፡

# ክፍል አራት

# ልዩ ልዩ ቅፆች

## 9. የግምት መገልገያ ቅፆች

1/ ት/ሲ/ግ/መ/ቅ-1

ቁጥር፡-----------------------------------
ቀን፡-------------------------------------
የደረሰኝ ቁጥር፡-------------------------

የተሽከርካሪ መሸጫ ዋጋ መገመቻ ቅፅ፡-

| | | | |
|---|---|---|---|
| **ሀ. ተዋዋዮች መረጃ** | | | |
| ተዋዋዮች | | ስም | አድራሻ ቀ/ወ/ክ/የቤ/ቁ |
| 1. | ባለንብረት | | |
| 2. | ውል ሰጪ | | |
| 3. | ውል ተቀባይ | | |
| **ለ. የተሽከርካሪው (የመሳሪያው) መለያዎች** | | | |
| መረጃ | | ከሊብሬ | የቴክኒክ ምርመራ |
| 4. | ሰሌዳ ቁ. | | |
| 5. | ሞተር ቁ. | | |
| 6. | ሻንሲ ቁ | | |
| 7. | የጭነት መጠን | | |
| 8. | የአገልግሎት ዘርፍ | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| **ሐ. የግምት መረጃዎች** | | | | | | |
| | ታሳቢ | ነጥብ | | ታሳቢ | መረጃ | ነጥብ |
| 9. | አጠቃላይ ተመራጭነት<br>ጨ = ዓ X አገ | | 9.1 | ፋብሪካ/ፋ/ | | |
| | | | 9.2 | ሀገር/ሀ/ | | |
| | | | 9.3 | አገልግሎት/አገ/ | | |
| 10. | ከእርጅና ቀሪ ዋጋ /እ/ | | 10.1 | የአገ.ዘመን/ዘ/ | | |
| | | | 10.2 | የገባበት ዓ/ም | | |
| 11. | የዋጋ ግሽበት /ግ/ | | | | | |
| 12. | የመነሻ ዋጋ /ዲ/ | | | | | |
| 13. | የመሸጫ ዋጋ ግምት<br>ዋ = (ዲ + (ዲX15%)) X ጨ X ግ X እ | | | | | |
| 14. | በተዋዋዮች የቀረበው ዋጋ | | | | | |
| 15. | የመጨረሻ ዋጋ ግምት | | | | | |
| 16. | ውል ሰጪ /ሻጭ/ ከዚህ በፊት የገዛበት ዋጋ | | | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **መ. ያረጋገጠው አካል** | | | | |
| | ያረጋገጠው | ስም | ፊርማ | ቀን |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 17. | የግምት ፀሐፊ | | | |
| 18. | ቴክኒሻን 1 | | | |
| | ቴክኒሻን 2 | | | |
| 19. | የግምት ሰራተኛ | | | |
| 20. | የግምት ኃላፊ | | | |

2/ ት/ሲ/ግ/መ/ቅ-2

ቁጥር፡-------------------------------

ቀን፡-----------------------------------

የደረሰኝ ቁጥር፡-----------------------

አደጋ የደረሰባቸው ተሽከርካሪዎች የመሸጫ ዋጋ መገመቻ ቅፅ፡-

<table>
<tr><td colspan="7">ሀ. ተዋዋዮች መረጃ</td></tr>
<tr><td colspan="2">ተዋዋዮች</td><td colspan="3">ስም</td><td colspan="2">አድራሻ ቀ/ወ/ክ/የቤ/ቁ</td></tr>
<tr><td>1.</td><td>ባለንብረት</td><td colspan="3"></td><td colspan="2"></td></tr>
<tr><td>2.</td><td>ውል ሰጪ</td><td colspan="3"></td><td colspan="2"></td></tr>
<tr><td>3.</td><td>ውል ተቀባይ</td><td colspan="3"></td><td colspan="2"></td></tr>
<tr><td colspan="7">ለ. የተሽከርካሪው (የመሳሪያው) መለያዎች</td></tr>
<tr><td colspan="2">መረጃ</td><td colspan="3">ከሊብሬ</td><td colspan="2">የቴክኒክ ምርመራ</td></tr>
<tr><td>4.</td><td>ሰሌዳ ቁ.</td><td colspan="3"></td><td colspan="2"></td></tr>
<tr><td>5.</td><td>ሞተር ቁ.</td><td colspan="3"></td><td colspan="2"></td></tr>
<tr><td>6.</td><td>ሻንሲ ቁ</td><td colspan="3"></td><td colspan="2"></td></tr>
<tr><td>7.</td><td>የጭነት መጠን</td><td colspan="3"></td><td colspan="2"></td></tr>
<tr><td>8.</td><td>የአገልግሎት ዘርፍ</td><td colspan="3"></td><td colspan="2"></td></tr>
<tr><td colspan="7">ሐ. የግምት መረጃዎች</td></tr>
<tr><td></td><td>ታሳቢ</td><td>ነጥብ</td><td></td><td>ታሳቢ</td><td>መረጃ</td><td>ነጥብ</td></tr>
<tr><td rowspan="3">9.</td><td rowspan="3">አጠቃላይ ተመራጭነት<br>ጨ = ዓ X አገ</td><td rowspan="3"></td><td>9.1</td><td>ፋብሪካ/ፋ/</td><td></td><td></td></tr>
<tr><td>9.2</td><td>ሀገር/ሀ/</td><td></td><td></td></tr>
<tr><td>9.3</td><td>አገልግሎት/አገ/</td><td></td><td></td></tr>
<tr><td rowspan="2">10.</td><td rowspan="2">ከእርጅና ቀሪ ዋጋ /እ/</td><td rowspan="2"></td><td>10.1</td><td>የአገ.ዘመን/ዘ/</td><td colspan="2"></td></tr>
<tr><td>10.2</td><td>የገባበት ዓ/ም</td><td colspan="2"></td></tr>
<tr><td>11.</td><td>የይዘት ተቀናሽ መጠን /ይ/<br>ይ = (እ-0.250) x በ</td><td></td><td>11.1</td><td>የገማች ኮሚቴ ነጥብ በመቶኛ /በ/</td><td colspan="2"></td></tr>
<tr><td>12.</td><td colspan="2">የዋጋ ግሽበት /ግ/</td><td colspan="4"></td></tr>
<tr><td>13.</td><td colspan="2">የመነሻ ዋጋ /ዲ/</td><td colspan="4"></td></tr>
<tr><td>14.</td><td colspan="4">የመሸጫ ዋጋ ግምት<br>ዋ = (ዲ + (ዲX15%)) X ጨ X ግ X (እ - ይ)</td><td colspan="2"></td></tr>
<tr><td>15.</td><td colspan="2">በተዋዋዮች የቀረበው ዋጋ</td><td colspan="4"></td></tr>
</table>

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 16. | የመጨረሻ ዋጋ ግምት | | | |
| 17. | ውል ሰጪ /ሻጭ/ ከዚህ በፊት የገዛበት ዋጋ | | | |
| መ. ያረጋገጠው አካል | | | | |
| | ያረጋገጠው | ስም | ፊርማ | ቀን |
| 18. | የግምት ፀሐፊ | | | |
| 19. | ቴክኒሻን 1 | | | |
| | ቴክኒሻን 2 | | | |
| 20. | የግምት ሰራተኛ | | | |
| 21. | የግምት ኃላፊ | | | |

3/ ት/ሲ/ግ/መ/ቅ-3

ቁጥር፡-----------------------------------

ቀን፡--------------------------------------

የገማች ኮሚቴ የተሽከርካሪ የይዞታ ነጥብ መስጫ ቅፅ፡-

| ተ.ቁ | የተሽከርካሪ ዋና ዋና አካላት | ከመቶ የሚኖረው ከፍተኛ ዋጋ | በአደጋ ምክኒያት ያጣው ነጥብ |
|---|---|---|---|
| 1. | ሞተር (Engine) | 25% | |
| 2. | የሀይል አስተላላፊ ክፍሎች (Power Train) | 20% | |
| 3. | የሻንሲ ሁኔታ (Chassis) | 32% | |
| 4. | የውጭ አካል ገጽታ (Body) | 15% | |
| 5. | የኤሌክትሪክ ክፍሎች ገቢና ውስጥ ያሉ መሣሪያዎችን ጨምሮ | 8% | |
| ጠቅላላ ድምር | | 100% | |

| የተሽከርካሪው መለያዎች | መረጃ | የተቀየረ ከሆነ አዲሱ ቁጥር |
|---|---|---|
| የሻንሲ ቁጥር | | |
| የሞተር ቁጥር | | |

አስተያየት..........................................................................................................

..........................................................................................................................

.....................................................................................::

| የባለሙያ ስም | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|
| 1. .................................. | .................. | ............... |
| 2. .................................. | .................. | ............... |
| 3. .................................. | .................. | ............... |

4/ ት/ሲ/ግ/ማ/ቅ-4

ቁጥር፡---------------------------------
ቀን፡-----------------------------------

በአብክመ ትራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ ባለስልጣን የተሽከርካሪ ግዥና ሽያጭ የግምት ዋጋ የሚያሳይ ቅጽ፡-

ለ ______________________________ፋይናንስ

<u>ባህር ዳር</u>

1. የባለንብረቱ ስም ……………………………………
2. የሰሌዳ ቁጥር ………………………………………
3. የአገልግሎት ዘርፍ …………………………………
4. የመጫን ችሎታው …………………………………
5. የሞተር ቁጥር ………………………………………
6. የሻንሲ ቁጥር ………………………………………
7. ከዚህ በፊት የመጨረሻ የተሽከርካሪው የተገመተበት ዋጋ ብር

   /____________________________________________/

8. አሁን የተሽከርካሪው የተገመተበት ዋጋ ብር

   /____________________________________________/

ያዘጋጀው ሠራተኛ ፊርማ …………..

የኃላፊው ፊርማ …………..

ቀን …………..

# ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

10. **በዚህ መመሪያ ያልተሸፈኑ ጉዳዮች አግባብነት ባላቸው ሌሎች መመሪያዎችና ህጎች የሚሸፈኑ ይሆናሉ፡፡**

11. **ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች አሰራሮች በተመለከተ**

ይህንን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም ሌላ መመሪያ ወይም የተለመደ አሰራር በዚህ መመሪያ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

12. **መመሪያውን ስለማሻሻል**

ይህን መመሪያ የባለስልጣኑ መ/ቤት አስፈሊጊ ሆኖ ሲያገኘው ሲያሻሽለው ወይም ሊሽረው ይችላል፡፡

13. **የመመሪያው ተፈፃሚነት**

1/ ይህ መመሪያ ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ የፀና ነው፤
2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተገለጸው ቢኖርም ይህ መመሪያ እንደገና አዲስ ቁጥር ከተሰጠበት ቀን በኂላ የሚነሳ መብት ወይም ግዴታ ህጋዊ ውጤት የሚኖረው መመሪያው በፍትህ ቢሮ ተመዝግቦ በአስተዳደር ተቋሙ ድረ-ገጽ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡

**ዘውዱ ማለደ በላይ**
**የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት**
**ትራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ ባለስልጣን**
**ዋና ዳይሬክተር**